አንበሳ ባንክ
anbesa bank
እንጸምረው • LET'S GO FOR IT

ለአንበሳ ባንክ አ.ማ ባለአክስዮኖች በሙሉ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምርጫ ሂደትና መስፈርቶች ለማሳወቅ የወጣ ማስታወቂያ

አንበሳ ባንክ አ.ማ 22ኛ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ቅዳሜ ነሐሴ 2 ቀን 2018 ዓ.ም ከጧቱ 2:30 ሰዓት ጀምሮ በአደዋ ሙዚየም በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 1360/2017 አንቀፅ 14 (2 እና 3)፣ መሰረት ይካሄዳል። በዕለቱ ባንኩን ለቀጣይ ሶስት ዓመታት የሚመሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ይከናወናል። ስለሆነም ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እጩ ሆነው መቅረብና መመረጥ የሚችሉት የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን የሚገባቸው መሆኑን ባንኩ በአክብሮት ያሳውቃል።

1. ከባለአክሲዮኖች ለሚጠቆሙና ለሚመረጡ ዕጩ የቦርድ ዳይሬክተሮች:-

1.1 ቢያንስ ለሁለት አመት የባንኩ ባለአክሲዮን የነበረ/ች፤
1.2 ባንኩን በቦርድ አባልነት ለማገልገል ፍቃደኛ የሆነ/ች፤
1.3 የሌላ ማንኛውም ባንክ ሰራተኛ ያለሆነ/ች፤
1.4 ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ወይም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው/ት፤
1.5 በቢዝነስ ማኔጅመንት፤ በባንኪንግ እና/ ወይም ፋይናንስ፣ የሂሳብ አያያዝ፣ በሕግ፣ ሪስክ ማኔጅመንት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በመሳሰሉት የትምህርት ዘርፎች ቢያንስ ሰባት (7) አመት የስራ ልምድ ያለው/ ያላት፤
1.6 የሌላ ፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ያልሆነ/ች፤
1.7 ታማኝና ሀቀኛ የሆነ/ች እንዲሁም መልካም ዝና እና ስነምግባር ያለው/ላት፤
1.8 የሕዝብ ጥቅም ለመጠበቅ የወጣ ሕግ በመተላለፍ በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ተከሶ/ሳ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት/ባት የማያውቅ/የማታውቅ፤
1.9 በራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት በሚመለከት ለሕዝብ መገለጽ ያለበትን መረጃ ደብቆ/ቃ የማያውቅ/ታውቅ፣ ሐሰተኛ የሂሳብ መግለጫ አቅርቦ/ባ የማያውቅ/የማታውቅ፣ የተቆጣጣሪ አካላትን ውሳኔ ላለመቀበል ወይም ላለመገዛት እምቢተኛ ሆኖ/ና የማያውቅ/የማታውቅ፤
1.10 እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ተመርምሮ እምነት በማጉደል፣ በማጭበርበር ወይም በተመሳሳይ ጥፋት በተቆጣጣሪ አካል፣ በፍ/ቤት ወይም ትራይቡናል የዲስፒሊን እርምጃ፣ እገዳ ወይም ቅጣት ተላልፎበት/ባት የማያውቅ፤
1.11 በራሱ/ሷ ወይም በዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ሥራ አስፈፃሚ በሆነበት/ችበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት/ባት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልሰጠበት/ባት፣ በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ/ቷ የዕዳ ማቻቻያ ያልተወሰደበት/ባት፤
1.12 እራሱ/ሷ ወይም የዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ሥራ አስፈፃሚ የሆነበት/ችበት ድርጅት የባንክ ወይም ሌላ ብድር ወይም ታክስ ላለመክፈሉ/ሏ ንብረቱ/ቷ በአራጅ ያልተሸጠበት/ባት፤
1.13 እራሱ/ሷ ወይም ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈፃም ወይም ሥራ አስፈፃሚ የሆነበት/ች ወይም ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ/ሏ ብድሩ ላለፋት ሁለት አመታት ውስጥ ጤናማ ያልሆነ ምድብ ውስጥ ገብቶበት/ባት የማያውቅ፤
1.14 ባለአክሲዮኑ/ኗ አክሲዮን የገዛበትን/ችበትን ገንዘብ ያገኘው/ችው ከከሰረ ሰው ወይም በአስተዳደር ችግር ምክንያት ኪሳራ ካጋጠመው ሰው ያልሆነ ወይም ገንዘቡን ያገኘው/ችው በማጭበርበር ወይም በሕገ ወጥ መንገድ ያልሆነ፤

1.15 ባለአክሲዮኑ/ኗ የአክሲዮኑ ባለቤት የሆነ/ች ጊዜ የነበረው/ራት የሀብት መጠን ከአክሲዮኖቹ ዋጋ በላይ የነበረ፤
1.16 በቂ ስንቅ/ገንዘብ ሳይኖረው/ራት ቼክ ሰጥቶ/ታ ሂሳብ በኢትዮጵያ ባንክ መመሪያ ባንክ መሠረት ያልተዘጋበት/ባት፤
1.17 በሌሎች ከአራት በበለጡ ተቋማት ውስጥ የቦርድ አባል በመሆን በማገልገል ላይ የማይገኝ /የማትገኝ፤ እንዲሁም
1.18 ከዚህ በፊት በንግድ ማህበር አደራጅነት ዳይሬክተርነት ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድቲሰሩ ከኃላፊታቸው ጋር የተያያዘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት ወይም በውብድና ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኝነታቸው ያልተረጋገጠ፤ መሆን ይገባቸዋል።
1.19 የሚጠቆመውና የሚመረጠው የቦርድ አባል ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው ሰው ማንነት መታወቅና ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል።
1.20 ከላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች ድርጅቶችን ወክለው በሚመረጡ የቦርድ አባላት ወይም ተፈፃሚነት አላቸው።

2. ለገለልተኛ እጩ የቦርድ ዳይሬክተሮች:-

2.1 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችና በሕግ የተቀመጠውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ገለልተኛ እጩ ዳይሬክተሮች በዳይሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው አስመራጭ ኮሚቴው አማካይኝነት ለምርጫ የሚቀርብ ይሆናል።
2.2 በ21ኛው አመታዊ መደበኛ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በዕጩነት የቀረቡት ገለልተኛ ዳይሬክተሮች በብሔራዊ ባንክ የተቀመጡ መስፈርቶችን እስካሟሉ ድረስ በዕለቱ ለምርጫ ይቀርባሉ።

ማሳሰቢያ

- አንድ ባለአክሲዮን እራሱን በእጩነት መጠቆም ይችላል፤
- ቢያንስ ሁለት ሴቶች በቦርድ አባልነት መመረጥ አለባቸው፤
- የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በቦርድ አባልነት መመረጥ አይችሉም፤
- ሶስት አመት ያገለገሉ ነባር የቦርድ አባላት በድጋሚ መመረጥ ይችላሉ፤
- የባንኩ የቦርድና የማኔጅመንት አባላት እንዲሁም የባንኩ ሠራተኞች ባለአክሲዮኖችን ወክለው ድምጽ መስጠት አይችሉም፤
- በእለቱ አምስት አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ የሚመረጥ ሲሆን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና የባንኩ ሠራተኞች የኮሚቴው አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም፤
- ከሚመረጡ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቢያንስ ሁለቱ ተደማጭነትየሌላቸው ባለአክሲዮኖች መሆን ይኖርባቸዋል።
- በባንኩ መመሥረቻ ፅሁፍ መሰረት የሚመረጡት ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር አስራ አንድ (11) ሲሆን ምርጫውም ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች ተጠቁመው የሚመረጡ (ምድብ 1)፣ በሁሉም ባለአክስዮኖች ተጠቁመው የሚመረጡ (ምድብ 2) እንዲሁም ሥራ ላይ ባለው ቦርድ ተመልምለው በሁሉም ባለአክስዮኖች የሚመረጡ ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን (ምድብ 3) በመምረጥ በሶስት ቡድን ተከፍሎ በቅደም ተከተል የሚከናወን ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ